# የተወላጅነት ፡ (የዜግነት) ፡ ሕግና ፡ አሠራሩ ፤

## ከፋሲል ፡ ናሆም*

ምንም ፡ እንኳ ፡ ዜግነት ፡[1] (ተወላጅነት) ፡ በተቀዳሚ ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ (ብሔራዊ) ፡ ዕንስ ፡ ሀሳብ ፡ ክልክ ፡ ውስጥ ፡ ያለና ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ የሚ ዳኝ ፡ ቢሆንም ፡ ዜግነትን ፡ የሚመለከቱት ፡ ሕጎች ፡ የብሔራዊነት ፡ ጠባይ ፡ (ተፈጥሮ) ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ በተጨማሪም ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ የሚጋጩ ፡ ናቸው ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የሚነሱት ፡ ችግሮች ፡ አያሌና ፡ የተማቱ ፡ ናቸው ። በአሁኑ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሁኔታዎች ፡ የተነሳ ፡ ሁለቱ ፡ ዋነኛ ፡ የችግሮች ፡ ምድቦች ፡ ዜግነት ፡ አልባነትና ፡ ጥንድ ፡ ዜግነት ፡ ናቸው ። የዜግነት ፡ አልባነት ፡ ውጤት ፡ በግለ — ሰቦች ፡ ወይም ፡ ክፍሎች ፡ የኛ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በሚገምቱትና ፡ ጠባቂ ፡ በመ ሆን ፡ ከሚጠቅማቸው ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ያላቸውን ፡ ቁራኛ ፡ ስለሚያለያየውና ፡ (ስለሚ ነጣጥለው) ፤ (ምክንያቱም ፡ እራሳቸውን ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ ስለሚያዛምዱ) ፡ እን ዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ጥንድ ፡ ዜግነት ፡ ከአንድ ፡ ለበለጡ ፡ አገሮች ፡ ተገዥነትን ፡ እንዲ ቀበሉ ፡ ማስገደዱ ፡ ነው ። በብሔራዊ ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሲዮናል ፡ ሁከት ፡ ጊዜም ፡ የነዚሁ ፡ ግለ—ሰቦች ፡ ወይም ፡ ክፍሎች ፡ መጎሳቆል ፡ መፍትሔ ፡ ሳይገኝለት ፡ ቀርቷል ።

ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ (አንቀጽ) ፡ ያህል ፡ ዜግነት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በአንድ ፡ ግለ— ሰብና ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ የተገዥነት ፤ የጠባቂነትና ፡ (የመከታነትና) የዝ ምድናን ፡ ግንኙነት ፡ ያመለክታል ፡ ዜግነት ፡ ከድርጊትና ፡ ከምኞት ፡ (ፍላጎት ፡) የሚገኝ ፡ አቋም ፡ ሲሆን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከሚደረገው ፡ አገል ግሎት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ መካፈልን ፡ ይጠይቃል ።[1ሀ] 'ሀ' በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ (በዚህ ፡ ዓለም ውስጥ) እያሌ ፡ የዜግነት ፡ ማግኛ ፡ መንገዶች ፡ አሉ ። ይሁንና ፡ በሁለት ፡ ሰፋ ፡ ባሉ ፡ መደቦች ፡ ሊከፈሉ ፡ ይችላሉ ፤ እነሱም ፡ ትውልድና ፡ በመቀባት ፡ መዜግ ፡ ናቸው ። ሁለቱ ፡ በትውልድ ፡ ዜግነት ፡ የሚወሰኑት ፡ መሠረታዊ ፡ የአቀራረብ ፡ ስልቶች ፡ <u>ዮስ ፡ ሶሊና</u> ፡ (በውልደት ፡ ዜግነት) ፡ <u>ዮስ ፡ ሳይንጕይኒስ</u> ፡ (በደም ፡ ዜግነት) ፡ ናቸው ። በመጀመሪያው ፡ ስልት ፡ መሠረት ፡ "ሀ" በተሰኘ ፡ አገር ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ ቤተሰቦቹ ፡ የ"ሀ" ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ቢሆኑም ፡ ባይሆኑም ፡ የ"ሀ" ፡ አገር ፡ ዜጋ ይሆናል ። ለአንድ ፡ ሕፃን ፡ የዜግነቱ ፡ መሠረት ፡ ከቤተሰቦቹ ፡ ዜግነት ፡ ይልቅ ፡ የት ውልድ ፡ ሰፍራው ፡ በመሆኑ ፡ የተነሳ ፡ ከ"ሀ" ፡ አገር ፡ ውጭ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከ"ሀ" ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ የ"ሀ" ን ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ አያገኝም ፡ (አይቀዳጅም) ፤

---

* በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ መምህር ፡ (ሌክቸረር) ።

1. ምንም ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ በኩል ፡ "ዜግነት ፡" የሚለውን ፡ ቃል ፡ የፈጸራሉን ፡ ተወላጅ ነት ፡ ከኤርትራውያን ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ ለማነፃፀር ፡ ብንጠቀምበትም ፡ "ተወላጅነት ፡" የሚለው ፡ አነጋገር ፡ በጠቅላላው ፡ ተጠቅመንበታል ።

1ሀ. አገር ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ የሚያመለክተው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ የምድር ፡ ክፍል ፡ የተለ የና ፡ ነፃ ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት ፡ ሲሆን ነው ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ በ "ሀ" አገር ፡ ውስጥ ፡ ከ "ሀ" አገር ፡ ዜጎች ፡ ወይም ፡ ከውጭ አገር ፡ ዜጎች ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ የ "ሀ" አገር ፡ ዜጋ ፡ ይሆናል ። በዮስ ፡ ሳንጉይኒስ (በደም ፡ ዜግነት ) መሠረት ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ በየትም ፡ አገር ፡ ቢወለድ ፡ የሚይዘው ፡ የቤተሰቡን ፡፤(የወላጆቹን ፡) ዜግነት ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ አንድ ፡ የ"ለ" ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ካላቸው ፡ ቤተሰቦች ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ በ"ሀ" ወይም ፡ በ"ለ" ሀገር ፡ ቢወለድም ፡ እንኳ ፡ የ"ለ ሀገር ፡ ዜጋ ፡ ይሆናል ።

እነዚህ ፡ ሁለት ፡ መሠረተ—ሃሳቦች ፡ በፍጹም ፡ መልካቸው ፡ በሚገናኙበት ፡ ወቅት ፡ ሊጋጩ ፡ (ሊቃረኑ) ፤መቻላቸውን ፡ መገመት ፡ አዳጋች ፡ አይደለም ፡ በ"ለ" ሀገር ፡ ከሚኖሩ ፡ ዜጎች ፡ የሚወለድ ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ የ"ሀ" ንም ፡ ሆነ ፡ የ"ለ" ን ፡ ሀገሮች ፡ ዜግነት ፡ አያገኝም ፡ ስለዚህም ፡ አገር - አልባ ፡ (ዜግነት ፡ የለሽ) ፡ ይሆናል ፤ በ"ሀ" አገር ፡ ከሚኖሩ ፡ የ"ለ" አገር ፡ ዜጎች ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ የሀ"" ንና ፡ የ"ለ"ን ሀገሮች ፡ ዜግነት ፡ ያገኛል ። ብዙዎች ፡ አገሮች ፡ የዜግነት ፡ ሕጋቸው ፡ ሁለቱንም ፡ መሠረተ—ሀሳቦች ፡ አጣምሮ ፡ በመያዝ ፡ አንዱን ፡ መሠረተ—ሀሳብ ፡ ከሌላው ፡ በማስበለጥ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ቢያመዝኑም ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ከሁለቱ ፡ በአንዱ ፡ ብቻ፡ በመፅናት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የዜግነት ፡ ሕጋቸው ፡ መወሰኛ ፡ ዓይነተኛ ፡ መሠረት ፡ (ምክንያት ፡) አድርገውታል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ አርጀንቲና ፡ በዮስ ፡ ሶሊ ፡ (በውልደት ዜግነት) በሚመሩ ፡ አገሮች ፡ ምድብ ፡ ውስጥ ፡ ስትሆን ፡ ጀርመን ፡ ግን ፡ የምትከተለው ፡ የወላጆችን ፡ ዜግነት ፡ የመወሰኛ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ። የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ (የዩናይትድ ፡ ስቴትስ) በመሠረቱ ፡ በትውልድ ፡ ሥፍራ፡ ላይ ፡ የምትመረኮዝ ፡ ስትሆን ፡ ፈረንሳይ ፡ ግን ፡ የሚቻላትን ፡ ያህል ፡ ዜጎች ፡ ለማግኘት ፡ በማቀድ ፡ በሁለቱም ፡ መሠረተ ፡ ሃሳቦች ፡ በሰፊው ፡ (የሚገባ) ፡ ትገላገላለች ፡ (ትጠቀማለች) ፡[2] የተሰበጣጠረው ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ የዜግነት ፡ መልክ ፡ በቅርብ ፡ ስያአገቡ ፡ ሴቶችና ፡ እንዲሁም ፡ ስለፆታዎች ፡ እኩልነት ፡[2ሀ] መሠረተ—ሀሳብ ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ በበለጠ ፡ ተስፋፍቷል ፡ (ተባብሷል) ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የዚህ ፡ ዓመት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታዎች ፡ አያሌ ፡ ሰዎችን ፡ አገር—አልባ ፡ አድርገዋቸዋል ፤ በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ስደተኞች ፡ የፖለቲካ ፡ ጠላት ፡ ናቸው ፡ በሚል ፡ የውንጀላ ፡ ሳቢያ ፡ አሰቃቂ ፡ (የከፋ) ፡ የተወላጅነት ፡ መግፈፊያ ፡ ሕግ ፡ በመውጣቱ ፡ ዜግነታቸውን ፡ ሊያጡ ፡ ችለዋል ።[3] ከጥንድ ፡ ዜግነትም ፡ የተነሳ ፡ የሚደርሱትን ፡ ግጭቶች ፡ በአገር—አልባነት ፡ እንደሚደርሰው ፡ ሁኔታ ፡ የከፉ ፡ ናቸው ፤ በጉዲፈቻ ፡ የማር ፡ ልጅ ፡ ማድረግ ፡ ሕፃናትን ፡ (ልጆችን)በደንብ ፡ ሕጋዊ ፡ ማድረግ፡ ጥንድ ፡ ዜግነትን ፡ አስከትለዋል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ አንዳንድ ፡ አቋሞች ፡፤(አገሮች) ዜጎቻቸው ፡ የቀድሞ ፡ ዜግነታቸውን ፡ ሳያጡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ እንዲያገኙ፡ ፈቅደዋል ። ታላቁ ፡ (ዋነኛው ፡) የጥንድ ፡ ዜግነት ፡ ችግር ፡ ደርሶ ፡ የነበረው ፡ ከሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊትና ፡ በዚያው ፡ በጦርነቱ ፡ ወቅት ፡ በተባበሩት የአሜሪካ ፡ መንግሥታት ፡ (በዩናይትድ ፡ ስቴትስ) ፡ ይኖሩ ፡ ከነበሩት ፡ ስደተኞች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ የወላጆቻቸውን ፡ የትውልድ ፡ ሀገር ፡ በመጎብኘት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡

---

2. እር ፡ ኤ ፡ ሌደለር ፡ ናሺናሊቲ ፡ ደሚላይል ፡ እንደዘ ፡ ፐርሶናል ፡ ሎው ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፤ የሚለውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም) ፤ ቮል ፡ ፮ ፡ ገጽ ፡ ፻፷፯ ፡ እና ፡ በኦፐንሃይም ፤ ኢንተርናሺናል ፡ ሎው ፡ (፰ኛ ፡ እትም ፡ ቦል ፡ ፩) ፡ ገጽ ፡ ፮፻፶፩ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ምርምር ፡ ተመልከት ።

2ሀ. ኢ ፡ ራቤል ፤ ዘኮንፍሊክት ፡ ኦቭ ፡ ሎውዝ ፡ ቦል ፡ ፩ ፡ (፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም) ፤ ገጽ ፡ ፻፴፩—፴፪ ፡ ይመለከቷል ።

3. ራቤል ፤ እዚያው ።

በወላጆቻቸው ፡ ዜግነት ፡ ምክንያት ፡ በነዚህ ፡ በሚኖሩባቸው ፡ አገሮች ፡ እንደዜጎች ፡ ተቆጥረው ፡ ለወታደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ በተመለመሉ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።[4]

ምንም ፡ እንኳ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ ውሎችና ፡ ፕሮቶኮሎች ፡ ለአንዳንዶቹ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ ቢሞክሩም ፡ ውጤታቸው ፡ እምብዛም ፡ አጥጋቢ ፡ አልነበረም ፤ ምናልባትም ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ዋነኛው ፡ ስለዜግነት ፡ ሕጎች ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ መቃረን ፡ (መጋጨት) ፡ እንደ ፡ ኤ. አ. የ፲፱፻፴ው ፡ የ"ሕግ" ስምምነት ፡ ሲሆን ፡ እሱም ፡ አገር—አልባነትና ፡ ጥንድ ፡ ዜግነትን ፡ ለማስቀረት ፡ በማለት ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተመሳሳይ ፡ (የተስተካከሉ) ሕጎችን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ መስክ ፡ ለሚገኙ ፡ ለብዙዎች ፡ ችግሮች ፡ ተመሳሳይ ፡ መልስ ፡ (መፍትሔ) ፡ ለማግኘት ፡ ባይቻልም ፡ በዚህ ፡ ጉባዔ ፡ የተደረገው ፡ የሀሳብ ፡ መለዋወጥና ፡ እንዲሁም ፡ በአንዳንድ ፡ ነጥቦች ፡ ላይ ፡ የተደረሰው ፡ ስምምነት ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ወደፊት ፡ ሄዷል ፡ ለማለት ፡ ያስችላል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ይኸው ፡ ስምምነት ፡ ለአንድ ፡ አንድ ፡ አገሮች ፡ የዜግነት ፡ ሕጎች ፡ ማለትም ፡ እ.ኤ.አ. ለ፲፱፻፴ው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ጭምር ፡ መሠረት ፡ ሆኗል ።

## የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ (የተወላጅነት) ፡ ሕግ ፤

በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ.ም. ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ—መንግሥት ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትንና ፡ (ተወላጅነትንና) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነዋሪነትን ፡ የሚያስጡትና ፡ (የሚያስገኙትና) ፡ የሚያሳጡት ፡ (የሚያስነፍጉት) ሁኔታዎች ፡ በሕግ ፡ ይወሰናሉ"[5] ይላል ። በዚህ ፡ ዓርእስት—ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በአገልግሎት ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ኤ.አ. በሐምሌ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ.ም. የወጣውና ፡ በመስከረም ፡ ፳፭ ፡ ፲፱፻፴ ፡ (እ.ኤ.አ.)[6] ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ (ተወላጅነት) ፡ ሕግ ፡ ነው ። ይህ ፡ በብሃርንና ፡ ሰላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡[7] ታትሞ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አጃም ፡ (ዝግጅት ፡ ቅንጅት) ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ነባር ፡ (ጥንታዊ) ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ ከአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ጥቂት ፡ ትርጓሚዎችን ፡ ከማቀናጀቱ ፡ (ከማስገባቱ) ፡ በስተቀር ፡ እንዳለ ፡ ሳይነካ ፡ ቀርቷል ። በ፲፱፻፷ ፡ ዓ. ም. (እ.ኤ.አ.) በወጣው ፡ በፍትሐ—ብሔርም ፡ ሕግ ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ የነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ክፍል ፡ በግልፅም ፡ ሆነ ፡ በስውር ፡ ስላልተሻረ ፡ ወይም ፡ ስለአልተሻሻለ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በሥራ ላይ ፡ ይውላል ።

### ሀ/ በመወለድ ፡ ዜግነት ፤

የዜግነቱ ፡ (የተወላጅነቱ) ፡ ሕግ ፡ የዩስ ፡ ሳንጒይኒስን ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ ሲገልጽ ፡ "ማንኛውም ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ (ዊት) ፡ የሆነ ፡ (ች) ፡ ሰው ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቢወለድ ፡ የኢትዮጵያ ፡

4. ሌድሰር ፤ እዚያው ።
5. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፱ ።
6. ሁለቱም ፡ ደንቦች ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ በአባሪ ፡ ሀና ፡ ለ ፡ ተገልብጠው ፡ ይገኛሉ ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ ተብሎ ፡ ካልተገለጸ ፡ በስተቀር ፡ በጠቅላላ ፡ ያውሮፓውያንን ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ እንከተላለን ።
7. ብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣው ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ደንቦች ፡ የሚወጡበት ፡ የመንግሥት ፡ መግለጫ ፡ ማውጫ ነበር ።

ዜጋ ፡ (ተገዥ) ፡ ይሆናል” ፡[8] ይላል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ካላቸው ፡ ወላጆች ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ (ልጅ) ፡ በየትም ፡ ሀገር ፡ ቢወለድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ ያገኛል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠቅላላው ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ በሚከተሉት ፡ አንቀጾች ፡ ተገድቧል ፡ (ተጠብቋል) ። ተከታዩ ፡ (ለጣቂው) ፡ ጠቅላላ ፡ መሠረተ—ሀሳብ ፡ “እያንዳንዱ ፡ ሕጋዊ ፡ ከሆነ ፡ ቅይጥ ፡ (ድብልቅ) ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ (ልጅ ፡ ...የአባቱን ፡ ዜግነት ፡ ይከተላል ፡ ይላል ፡[9] ስለዚህም ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ካላት ፡ እናትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ካለው ፡ አባት ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ (ልጅ) ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ ያገኛል ፤[10] እናቲቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ሆና ፡ አባትየው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ሕፃኑ ፡ የአባቱን ፡ ዜግነት ፡ ይከተላል ፡ ከሁለቱ ፡ ወላጆች ፡ አንዱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ከሆነ፡ ወላጆች ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ ያገኛል ፤ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነው ፡ አባት ፡ ኢትዮጵያዊቷን ፡ እናት ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በተደረገ ፡ ግንኙነት ፡ ልጅ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ መልሶ ፡ በሕግ ፡ ቢያገባት ፡ እንኳ ፡ የዜግነቱ ፡ ሕግ ፡ በተታዩ ፡ (በለጣቂው) ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ በደንብ ፡ ሕጋዊ ፡ የተደረገው ፡ ሕፃን ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነውን ፡ የአባቱን ፡ ዜግነት ፡ የሚከተለው ፡ የአባትዬው ፡ ሀገር ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ የውጭውን ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ከነተፈጥሮ ፡ መብቱ ፡ የሚያቀዳጀው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ፡ ነው ፡ ይላል ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ ሕፃኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ እንደያዘ ፡ ይቀራል ።[11]

አንድ ፡ ሕፃን ፡ የውጭ ፡ ዜግነት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ በጉዲፈቻ ፡ የማር ፡ ልጅ ፡ ሲሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ እንደያዘ ፡ ይቀራል ፤ እንደዚሁም ፡ በጉዲፈቻ ፡ የማር ፡ ልጅነት ፡ “የጉዲፈቻውን ፡ ልጅ ፡ የቀድሞ ፡ ዜግነት ፡ መለወጥ ፡ (መቀየር) አያመለክትም ፡ (ይለወጣል ፡ አያሰኝም)” ፡[12]

ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዩስ ፡ ሳንጉይኒስን ፡ መሠረት ፡ ሀሳብ ፡ በጥብቅ ፡ በመከተል ፡ የወላጆችን ፡ ዜግነት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ወሳኝ ፡ አግካኝ ፡ በማድረግ ፡ አገር—አልባነትንና ፡ ጥንድ—ዜግነትን ፡ ለማስወገድ ፡ ሞክራለች ፡ በተረፈ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተወልዶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ በመቀባት ፡ ከመቀበል ፡ ሌላ ፡ በተለየ ፡ ሁኔታ ፡ ዜግነትን ፡ ስለማግኘት ፡ ሕጉ ፡ አይናገርም ፡ (አይገልጽም) ።

## ለ/ ግለ—ሰብ ፡ በቅባት ፡ ስለሚያገኘው ፡ ዜግነት ፤

እስካሁን ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ዜግነትን ፡ የማግኛው ፡ አማራጭ ፡ መንገድ ፡ በመቀባት ፡ መዜግ ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ የሚሰጠው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ከአሟላ ፡ በኋላ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ማንም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡

---

8. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፩ ።
9. የኢትዮጵያ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፪ ።
10. በአንቀጽ ፡ ፯ ፡ መሠረት ፡ ፆ ፡ ልጅ ፡ የናቱን ፡ የመጀመሪያ ፡ ተወላጅነት ፡ ያላገኘ ፡ መሆኑን ፡ ከተጠየቀ ፡ ማስመስከር ፡ እንዳለበት ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ።
11. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፰ ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ አለመሆን ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ የማይታወቅ ፡ በመሆኑ ፡ ትውልድን ፡ ሕጋዊ ፡ ማድረግ ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ የለም ። መወለድ ፡ ብቻ፡ ከተረጋገጠ ፡ የወላጆች ፡ መጋባትና ፡ አለመጋባት ፡ልዩነት ፡ አያመጣም ። የኢትዮጵያን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ ፯ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ይመለከቷል ።
12. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ። በሌላው ፡ አንፃር ፡ ደግሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ የሆነ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተወላጅነት ፡ አያገኝም ።

ውስጥ ፡ ባንድነት ፡ ባዕድና ፡ ዜጋ ፡ እንዲሆን ፡ አይፈቀድለትም ፤ ዜጎቻቸውን ፡ ሌላ ተጨማሪ ፡ ሁለተኛ ፡ ዜግነት ፡ እንዲያገኙ ፡ የሚፈቅዱ ፡ አገሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዜጎቻቸው ፡ በሌላ ፡ ሀገር ፡ የመሥራትንና ፡ የባለንብረትነትን ፡ መብት ፡ ጥቅም ፡ እን ዳያጡ ፡ በማለት ፡ ሁለተኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ዜግነት ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ቢፈቅዱላቸውም ፡ በተቀዳሚ ፡ እንደራሳቸው ፡ ዜጋ ፡ አድርገው ፡ ይቆጥሯቸዋል ፡ (ይገምቷቸዋል) ።

አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ (እንደተለመደው) አንድ ፡ ሰው ፡ ዜግነት ፡ ከመሠጠቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ብዙ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎችን ፡ ማሟላት ፡ አለበት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ እነዚህ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በመጠን ፡ ይለያዩ ፡ እንጂ ፡ በጠቅላላ ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ናቸው ። በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ እነዚህ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ከዚህ የተዘረዘሩት ፡ ናቸው ።

"ማንኛውም ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጋ ፡

ሀ/ በአገሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለአካለ—መጠን ፡ (ለዓቅመ—ዓዳም) ከደረሰ ፡

ለ/ በትንሹ ፡ ከአምስት ፡ ዓመታት ፡ ያላነሰ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከኖረ ፡

ሐ/ ለራሱና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ የእለት ፡ ጉርስ ፡ የሚያስገኝ ፡ መተዳደሪያ ፡ ካለው ፡

መ/ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከቻለና ፡

ሠ/ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በኃጢአት ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ አለመቀጣቱን ፡ የሚ ያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ካቀረበ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ፡"[13]

በኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የውጭው ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ "በዜግነት፡ ሕግ ፡ ደንብ ፡ ለአካለ—መጠን" እንዲደርስ ፡ ያስፈልጋል ፡ ከሚል ፡ የተሳሳተ ፡ አስተሳሰብ ፡ የተነሳ ፡ "በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ—ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፰ ፡ መሠ ረት ፡ ዕድሜው ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ እንዲሆን ፡"[14] ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ ፍች ፡ ሊሰጥ ይችላል ። በዚህ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለዐቅመ—ዓዳም ፡ መድረስ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ቀላልና ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ከአንድ ፡ በልጅነቱ ፡ የተ ነሳ ፡ (ለመዋዋልና ፡) የውል ፡ ፈቃደኛ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ፡ ተብሎ ፡ በሀገሩ ፡ ከሚገመት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ተዋዋለች ፡ ተብላ ፡ እንዳትወቀስ ፡ (እንዳ ትወነጀል ፤ እንዳትከሰስ) ፡ በመፈለግ ፡ ነው ።

አብዛኛዎቹ ፡ የሕግ ፡ አቋሞች ፡ አካለ—መጠን ፡ በደረሱና ፡ ባልደረሱ ፡ መካከል፡ ልዩነት ፡ ስለሚያደርጉና ፡ በአንድ ፡ የሕግ ፡ አቋምና ፡ በሌላው ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ መካ ከል ፡ ያለው ፡ የዕድሜ ፡ ወሰን ፡ ልዩነት ፡ በጠቅላላው ፡ እምብዛም ፡ ስላልሆነ ፡ ይህ፡

13. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፪ ። ባንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ዘርፎች ፡ ውስጥ ፡ ለ(ለ) ፡ ለውጥ ፡ የሚፈለገው ፡ ሰውዬው ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥታቸው ፡ ሥር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መሬት ፡ ዕይ ፡ እንዲያገለግል ፡ ነው ። ዚኢንዲያን ፡ ኮድ ፡ (፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፡ ቮል. ፪ ፤ የ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዜግነት ፡ ደንብ ፡ (ሲቲዘኔሺፕ ፡ አክት) ፡ ከሚለው ፡ ጋር ፡ ያነፃፅሯል ።

14. ሴድለር ፤ እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፰፯ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ደንቦቹ ፡ ግልጽ ፡ ባይመስሉም ፤ ሕጉ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በሚያወሳበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግልጽ ፡ የሚጠቅስ ፡ መሆኑንና ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ አለመጥቀሱን ፡ ስናውቅ ፡ "እንዳገሩ ፡" ማለት ፡ "በአገሩ ፡ ሕገ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ ሳይሆን ፡ ለዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ "በራሱ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡" የሚል ፡ መሆኑ ፡ ነው ። (እንክሮው ፡ የተጨመረው ፡ በዚሁ ፡ ደራሲ ፡ ነው) ። ይህ ፡ የተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ሲሠራ ፡ የነበረው ፡ ትክክለኛ ፡ ባል ሆን ፡ ትርጉም ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ትክክለኛነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ባለመቻሉ ፡ ከሚከተለው ፡ የበለጠ ፡ ጉዳት ፡ ጋር ፡ ነው ።

አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚያስከትል ፡ አይመስልም ፡[15] መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ዋነኛው ፡ ነገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ አለመድረስ ፡ የዜግነት ፡ ማገጃ ፡ ገደብ ፡ ሲሆን ፡ ለአካለ—መጠን ፡ የደረሰ ፡ ብቻ ፡ በመቀባት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ሊሆን ፡ መቻሉን ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ አስፈላጊ፡ ሁኔታ ፡ በቂ ፡ ምክንያቱ ፡ በመቀባት ፡ ዜግነትን ፡ መቀበል ፡ በፈቃድ ፡ (በፍላጎት)፡ የተደረገ ፡ የሕግ ፡ ተግባር ፡ በመሆኑና ፡ ዋነኛ ፡ ሕጋዊና ፡ ተግባራዊ ፡ ውጤቶች ፡ ስለሚያስከትል ፡ ነው ።

ስለአምስት ፡ ዓመቱም ፡ የነዋሪነት ፡ አስፈላጊነት ፡ በግልጽ ፡ (በኦፊሲየል) ፡ እንደሚታወቀው ፡ ነዋሪነት ፡ በተቀዳሚ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ አገባብንና ፡ የአገሪቱን ፡ የይለፍ ፡ (የኢሚግሬሽን) ፡ ሕግ ፡ ደንቦችና ፡ ፎርማሊቲዎች ፡ ማሟላትን ፡ ይጠይቃል ፤ ስለዚህም ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ ለማግኘት ፡ ማመልከቻ ፡ የሚያቀርበው፡ አመልካች ፡ ከላይ ፡ የተገለፀውን ፡ የይለፍ ፡ ሕግ ፡ ከአፈረሰ ፡ የዜግነት ፡ ማግኛ ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ተከታታይና ፡ ልክ ፡ ከማመልከታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ መሆን ፡ አለበት ። የነዋሪነትም ፡ አስፈላጊነት ፡ ግልጾቹ ፡ መመሪያ ፡ ምክንያቶች ፡ በአንድ ፡ በኩል፡ የመንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የአመልካቹ ፡ ጠባይና ፡ ብቁነት ፡ ለመለካት ፡ (ለመፈተን) ፡ እንዲያስችላቸው ፡ ሲሆን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተውን ፡ ግለ—ሰብ ፡ ከአገሪቱ ፡ ሁኔታና ፡ ከሕዝቧ ፡ አኗኗር ፡ እንዲተዋወቅና ፡ እንዲዛመድ ፡ ለማስቻል ፡ ነው ። ባጭሩ ፡ ለአገሪቷም ፡ ሆነ ፡ ለግለ—ሰብ ፡ የሁለቱ ፡ ግንኙነት ፡ ተስማሚ ፡ መሆኑን ፡ ለመፈተን ፡ (ለመለካት) ፡ እንዲያስችላቸው ፡ ጊዜ ፡ ለመስጠት ፡ ነው ።

ግለ—ሰቡም ፡ እራሱንና ፡ ቤተሰቡን ፡ (ቤት ፡ ሰብ ፡ ካለው) ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚያስችለው ፡ ሥራ ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈለገው ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ ሲቀበል ፡ በሕብረ—ሰቡና ፡ በአገሪቱ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ሸክም ፡ እንዳይሆን ፡ ለማለት ፡ ነው ። የቋንቋ ችሎታውም ፡ (ብቁነቱም) ፡ የተስተካከለ ፡ መጠን ፡ ባላቸው ፡ ፈተናዎች ፡ ይረጋገጣል ። የአማርኛ ፡ ቋንቋም ፡ አስፈላጊነት ፡ መሠረተ ፡ ምክንያቱ ፡ ሊገለገሉበት ፡ የሚያስችል ፡ የአገሪቱ ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲዬል) ፡ የቋንቋ ፡ ችሎታ ፡ (ዕውቀት) ፡ ከሕብረተ—ሰቡ ፡ ጋር ፡ የመወሀድንና ፡ ያንድነትን ፡ ስሜት ፡ በመስጠቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በተጨማሪም፡ ሕብረተ—ሰቡን ፡ በተሻለ ፡ ለመርዳትና ፡ እንደዚሁም ፡ ጠቃሚ ፡ ሕይወትና ፡ ሕብረትን ፡ ለማስገኘት ፡ አስፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

የመጨረሻውም ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ "በወንጀል ፡ ወይም ፡ በኃጢአት ፡" ተከሶ ፡ አለመቀጣትን ፡ የሚያሳይ ፡ ማስርጃ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ አንቀጽ ፡ ከ፲፱፻፶፯ቱ ፡ (እ. ኤ. አ.) የኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ በመንጣጠር ፡ መገንዘብ ፡ አለበት ፤ ሲተረጎምም ፡ "ማለም ፡ ፐር ፡ ሴ" ወንጀሎች ፡ ማለት ፡ ሲሆን ፤ ይኸውም ፡ በተለምዶ ፡ ጥፋትነታቸው ፡ ታውቆ ፡ (ተረጋግጦ) ፡ የሚያስቀጡት ፡ ሕግ ፡ እንዳይደረጉ ፡ የከለከላቸውን ፡ ድርጊቶችና ፡ እንዲሁም ፡ ሕግ ፡ እንዲሠሩ ፡ ያዘዛቸውን ፡ አለመሥራትን ፡ ይመለከታል ። ይህ ፡ ትርጉም ፡ በደንብ ፡ ተላላፊ ፡ መቀጫ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የደንብ ፡ መተላለፍ ፡ አይጨምርም ፡ ምክንያቱም ፡ ደንብን ፡ በመተላለፍ ፡ ብቻ ፡ ዜግነትን ፡ መንፈግ ፡ (መከልከል) ፡ የማይፈለግና ፡ በቂ ፡

15. ችግር ፡ ሊፈጥሩ ፡ ከሚችሉት ፡ አንዱ ፡ ነገር ፡ ዜግነት ፡ አልባ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ነው ። በዚህ ፡ ነገር ፡ እንደሌላ ፡ አገሮች ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ የሚለው ፡ ሕገ ፡ አገባብ ፡ ስለሚኖረው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፺፰ ፡ ሊያገለግል ፡ ይችል ፡ ይሆናል ።

ምክንያት ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። መንግሥቱ ፡ የሚፈልገው ፡ የወንጀለኞችን ፡ ኅብረተ—ሰብ ፡ ጥርቅም ፡ ለማስወገድ ፡ ስለሆነ ፡ ከወንጀል ፡ ነፃ ፡ የመሆን ፡ አስፈላጊነት ፡ ወንጀልን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ደንብ ፡ መተላለፍን ፡ አይመለከትም ፤ በማጥም ፡ ማስረጃው ፡ በሰነድ ፡ መልክ ፡ ሆኖ ፡ በተገቢው ፡ ባለስልጣኖች ፡ መፈረም ፡ አለበት ፡ አመልካቹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የኖረ ፡ ስለሚሆን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አግባብ ፡ ካላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሰነዱን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረቡ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከቅጣት ፡ ነፃ ፡ መሆንን ፡ የሚያሳየው ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ሬጅስትራር ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ ማለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነዋሪ ፡ ከመሆን ፡ አስቀድሞ ፡ በሌሎች ፡ ሀገሮች ፡ የተፈጸሙ ፡ ወንጀሎችና ፡ ቅጣቶች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ አቀራረብ ፡ (አስተሳሰብ) ፡ አጥጋቢ ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቀድሞ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ወንጀል ፡ ቢፈፅምም ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ለአምስት ፡ ወይም ፡ ከአምስት ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ሰውዬው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በቆየባቸው ፡ ጊዜያቶች ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ ዜጋ ፡ መሆኑን ፡ እስከአሳየ ፡ ድረስ ፡ ነው ። የአምስቱን ፡ በቅባት ፡ ዜግነት ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስችሉትን ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋዋል ፡ ካጠና ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ዓቃቢ ፡ ሕግና ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ የነበረው ፡ ማርዩን ፡ በዝነኛው ፡ መጽሐፉ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።” “ብዙዎች ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ማንኛዎቹንም ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የሠፈሩትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ሳያሟሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ተሰጥተዋል” ከዚህም ፡ በመቀጠል ፡ ሲደመድም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ “የተባለው ፡ ሕግ ፡ ወይ ፡ ያለቅጥም ፡ ቀርቷል ፡ (አገልግሎቱን ፡ አቋርጧል) ፡ ወይም ፡ በፍጹም ፡ በሚገባ ፡ አልታወጀም ፤”[16] በርግጥ ፡ ሕጉ ፡ አገልግሎቱን ፡ አላቋርጠም ፤ ተገቢ ፡ እወጃም ፡ አልነደለውም ፤ ብቻ ፡ በመስከረም ፡ ፳፰ ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ (ኢ.ት. አ.) በወጣው ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ማሻሻያ ፡ አዋጅ ፡ በመሻሻሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አንዳንዶቹን ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ልቅ ፡ እንዲያደርግ ፡ (እንዲተው) ፡ አስችሏል ።

የማሻሻያው ፡ አዋጅ ፡ በከፊል ፡ እንዲህ ፡ ይነበባል ፡ “የኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የውጭው ፡ አገር ፡ አመልካች ፡ ለአገሪቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ከተገመተ ፡ ወይም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ (በተባለው ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ (ለ) ና (መ)) ያሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ባያሟላም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚያስችሉት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲኖሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ።” በአንቀጽ ፡ ፲፪(ለ) መሠረት ፡ አመልካቹ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ለአምስት ፡ አመታት ፡ የኖረ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ለአምስት ፡ ዓመታት ፡ ነዋሪነት ፡ አስፈላጊነት ፡ ከዋነኞቹ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ መንግሥቱ ፡ (አገሪቱ) ፡ የዚህን ፡ ግንኙነት ፡ ምቹነት ፡ (ብቁነት ፡ ተስማሚነት) ፡ ለመፈተን ፡ (ለመሞከር) ፡ እንዲያስችለው ፡ ከሆነና ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ግለሰብ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ሳይኖር ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ መመሪያ ፡ (ፖሊሲ) ፡ ትርጉሙን ፡ አጥቷል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የአገሪቱ ፡ የፖለቲካ ፤ የሰሻልና ፡ የኤኮኖሚ ፡ (የምጣኔ—ሃብት) ፡ ጥቅም ፡ የአምስት ፡ ዓመቱን ፡ የነዋሪነት ፡ አስፈላጊነት ፡ ለማስወገድ ፡ (ለማስቀረት) ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፲፪ትም ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ችሎታ ፡ (ዕውቀት) ፡ አስፈላጊነት ፡ ሊወገድ ፡ (ልቅ ፡ ሊሆን) ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡

16. ኤን ፡ ማሬን ፤ ዘኢትዮጵያን ፡ ኢምፓየር ፡ ፌደሬሽን ፡ እንድ ፡ ሎውዝ ፡ (፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ገጽ ፡ ፷፱። የተወላጅነቱን ፡ ሕግ ፡ የሚያሻሽለው ፡ አዋጅም ፡ በሌድለር ፡ ያልተጠቀሰ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከኖረና ፡ በብሔራዊ ፡ ዕድገት ፡ እንቅስቃሴ ፡ ውስጥ ፡ በመራዳትና ፡ በመተባበር ፡ ስሜቱን ፡ በሕብረተ—ሰቡ ፡ ከገለ ጸና ፡ የሕይወቱን ፡ (የኑሮውን) ፡ ጠቃሚነት ፡ ካሳወቀ ፡ አማርኛ ፡ ለማወቅ ፡ (ለመማር) ፡ ጊዜው ፡ ስላለፈበት ፡ (ቋንቋውን ፡ ባለመቻሉ) ፡ ብቻ ፡ (በተለይ ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ በመ ኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የቀድሞውን ፡ ዜግነቱን ፡ ያጣ ፡ ከሆነ) ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ሊነፈገው ፡ (ሊከለከል) ፡ አይገባም ። ደግሞ ፡ የአገሪቱ ፡ የሶሻል ፡ የኤኮኖሚና ፡ የፖለ ቲካ ፡ ጥቅሞች ፡ (ፍላጎቶች) ፡ ሊገመቱ ፡ (ሊታዩ ፡ ሊመዘኑ) ፡ ይገባቸዋል ።

የዜግነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ (ከአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፤ ከውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትርና ፡ ከአንድ ፡ ሌላ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ የተውጣጣ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ኮሚሽን ፡ ያቋቁማል ። ኰሚሺኑም ፡ በአመልካቹ ፡ አማካይነት ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒ ስቴር ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋር ፡ የሚቀርቡትን ፡ (የመታወቂያ) ፡ የመለያ ፡ ወረቀቶችና ፡ ከወንጀል ፡ ነፃ ፡ መሆንን ፡ የሚያሳየውን ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ጭምር ፡ የማመዛዘንና ፡ (የመፈተንና) ፡ ግዴታ ፡ ተጥሎበታል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሊገለፅ ፡ የሚገባው ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ ማመልከቻ ፡ ለመፍቀድ ፡ (ለመቀበል) ፡ ወይም ፡ ለመከልከል ፡ (ላለመቀበል)፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ኮሚሺኑ ፡ መሆኑንና ፡ አመልካቹም ፡ ራሱ ፡ በተገ ኘበት ፡ በኮሚሺኑ ፡ መደመጥ ፡ (መሰማት) ፡ እንዳለበት ፡ ነው ። ማመልከቻውም ፡ ተቀ ባይነትን ፡ ካገኘ ፡ አመልካቹ ፡ የተገኘነት ፡ ቃለ—መሃላውን ፡ በኰሚሺኑ ፡ ፊት ፡ ካደ ረሰ ፡ (ካደረገ) ፡ በኋላ ፡ ዜግነትን ፡ በመቀባት ፡ ይቀበላል ።

በሌሎች ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አቋሞች ፡ እንደሚደረገው ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በቅ ባት ፡ ዜግነትን ፡ መቀበል ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ—ሥርዓት ፡ ነው ።[17] በኮሚሺኑ ፡ የሚደረሰው ፡ ውሳኔ ፡ የመጨረሻና ፡ ይግባኝ ፡ የማይባልበት ፡ ነው ።[18] ከዚህም ፡ በላይ ፡ የውጭው ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ በመንግሥቱ ፡ (በአገሪቱ) ፡ የሚሰጠው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ዕድል ፡ የፀጋ ፡ ችሮታ ፡ ውለታ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጅ ፡ በሕገ—መንግሥቱ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩልነትና ፡ በሕግ ፡ በሚወሰነው ፡[19] የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ማግኘትና ፡ ማጣት ፡ አንፃር ፡ የዜግነት ፡ ሕግና ፡ አሠራሩ ፡ የተስተካከለ ፡ አተረጓጎምና ፡ አፈጻጸም ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

<u>በመቀባት ፡ ዜግነት ፡ ስለሚያገኝ ፡ ቤተሰብ ።</u>

መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ አስገራሚ ፡ ጉዳይ ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ የሚቀበ ለው ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ወዲያውኑ ፡ በባሏ ፡ ድርጊት ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ አለመሆኗና ፡ ይልቁንም ፡ እርሷው ፡ ራሷ ፡ ማመልከት ፡ እንዳለባት ፡ ማስፈለጉ ፡ ነው ።[20] ሕጉ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ስላልደረሱ ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ ከተቀበለው ፡ ሰው ፡ ስለተ ወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ አቋም ፡ ምንም ፡ አይናገርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የነሱን ፡ ሁኔታ ፡ ከሚስ ቲቱ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ በማመሳሰል ፡ እነርሱ ፡ ራሳቸው ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ሲደርሱ ፡

17. ብዙ ፡ አገሮች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ያላቸው ፡ አመለካከት ፡ ይለያያል ። ለምሳሌ ፡ በአሜሪካ ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚወሰን ፡ ነገር ፡ ነው ። ከርፐስ ፡ ጁለስ ፡ ሴኮንዶም ፤ (፲፱፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ቮል. ፫ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፺፬ ፡ ይመለከቷል ።

18. ይህ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ልዩ ፡ ሥልጣኑን ፡ በመጠቀም ፡ ተወላጅነት ፡ መስጠቱን ፡ አይከለክለውም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ይመለከቷል ።

19. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፤ አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡ እና ፡ ፴፱ ።

20. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፮ ። በይበልጥም ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ የሆነችው ፡ ሴት ፡ ባል ፡ እንዲሁ ፡ ሚስቱን ፡ ተከትሎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ፡ አይችልም ። (የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ እና ፡ ፭ ፡ ተመልከት ።)

ማመልከት ፣ አለባቸው ፡ በማለት ፡ ለመደምደም ፡ ይቻላል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በቲዎሪ ፡ ኮሚሺኑ ፡ ከአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ለአንዳንዶቹ ፡ የቤተ—ሰብ ፡ አባሎች ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ እንዲቀበሉ ፡ ቢፈቅድና ፡ ሌሎቹን ፡ አባሎች ፡ ሊከለክል ፡ ቢችልም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ዓላማ ፡ ጥንድ ፡ ዜግነትና ፡ አገር ፡ አልባነትን ፡ ለማስወገድ ፡ በመሆኑ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ መፈጠሩ ፡ አጠራጣሪ ፡ ቢመስልም ፡ ጉዳዩ ፡ በሚመለከተው ፡ ቤተሰብ ፡ ላይ ፡ የማያስፈልግ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ሁኔታዎችን ፡ መፍጠር ፡ የለበትም ። በቤተ ፡ ሰቡ ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ የባልና ፡ የአባትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የማግኘት ፡ ውጤት ፡ እንደ—አንድ ፡ ዋነኛ ፡ ሁኔታ ፡ መገመት ፡ ሲገባው ፡ በቤተሰቡም ፡ አባሎች ፡ የተለያዩ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ይቅረቡ ፡ እንጅ ፡ ቤተሰቡ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አካል መታየት ፡ አለበት ።[21]

አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ዜግነቱን ፡ ካገኘበት ፡ ጊዜ ፡ በማከታተል ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ካላት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻን ፡ የፈፀመ ፡ እንደሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ሴቲቱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ ትቀዳጃለች። ይህም ፡ አንቀጽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የተወሰነ ፡ መግለጫ ፡ (ቅጽል) ስለማይሰጠው ፡ ቃሉ ፡ የውልደት ፡ ዜግነትና ፡ የቅባት ፡ ዜግነትን ፡ ያጠቃልላል ። የዜግነቱ ፡ ሕግ ፡ [21ሀ] ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የሚተረጉምበት ፡ መሥመር ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ በየት ፡ ሥፍራ ፡ እንደተፈጸመና ፡ ከተጋቢዎቹ ፡ የትኛው ፡ ወገን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ እንዳለው ፡ በመመልከት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ስለ ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ከዚህ ፡ የተለየና ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ፅንሰ—ሃሳብ ፡ ያለው ፡ በመሆኑና ፡ ይህም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ፍላጎት ፡ (ምኞት) ፡ የሚገልጽ ፡ በመሆኑ ፡ በዚህ ፡ መሥመር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በዜግነቱ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ የበላይነት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ ይቻላል ።[22]

በአንቀጽ ፡ ሁለት ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ እንደተጋባች ፡ ወዲያውኑ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ብቁ ፡ ትሆናለች ። ይሁንና ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ እራሱን ፡ በራሱ ፡ የሚያስፍጽም ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ ይህችን ፡ ሴት ፡ ከሌላው ፡ ዜግነቷ ፤ በተጨማሪ ፡ (ይህች ፡ ሴት ፡ የቀድሞውን ፡ (ሌላውን) ፡ ዜግነቷን ፡ እንደያዘች ፡ ለመቅረት ፡ የፈቀደች ፡ እንደሆነና ፡ ለዚህም ፡ የሌላው ፡ ሀገር ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ የሚፈቅድ ፡ ከሆነ) ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ እንድትቀበል ፡ ያስገድዳታል ስለሚያሰኝ ፡ የጥንድ ፡ ዜግነትን ፡ ችግር ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ። በአንቀጽ ፡ ፪ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ "የቀድሞ ፡ የናቱ ፡ ዜግነት፡" የተጠቀሰውን ፡ በማየት ፡ (በመገመት) ፡ (በመገንዘብ) ፡ ሌላውን ፡ ዜግነቷን ፡ እንደያዘች ፡ ብትቀርም ፡ ባትቀርም ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ እራሱን፡ በራሱ ፡ የሚያስፈጽም ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ መደምደሚያ ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ (ለማፍረስ) ፡ በትንሹ ፡ አዳጋች ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። እንደተባለው ፡ ከሆነ ፡ እንደዚሁ ፡ ያለችው ፡ ሴት ፡ "ጥንድ ፡ ዜግነት ፡ ሊኖራት ፡ ይችላል ፤. . . ይህም ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ከባሏ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ዜግነት ፡ ቢኖራት ፡ ተፈላጊ ፡ (ተወዳጅ)፡

---

21. የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሌላ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቶች ፡ ዘንድ ፡ ያልታወቀውን ፡ ስለቤተሰብ ደህንነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። አንቀጽ ፡ ፵፰ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። "የኢትዮጵያውያን ፡ ቤተሰብ ፡ በሕጋዊ ፡ ልዩ ፡ ጥበቃ ፡ የሚጠበቅ ፡ ነው" ።

21ሀ. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ እና ፡ ፳ ።

22. ስለኢትዮጵያ ፡ የጋብቻ ፡ ሕግ ፡ ደምበኛ ፡ ምርምር ፡ በዊልያም ፡ ቡሕሺያር ፡ የተጻፈ ፡ ማሬጅ ፡ አንደር ፡ ዘሲቪል ፡ ኮድ ፡ ኦቭ ፡ ኢትዮጵያ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡) ፤ ቮል. ፩ ፡ ገጽ ፡ ከ፫፻—፫፱ ፡ ድረስ ፡ ተመልከት ።

(የሚፈለግ) ፡ ነው ።[23] ሴትዮዋ ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ጥንድ ፡ ዜግነት ፡ እያላት ፡ ከባሏ ፡ ጋርም ፡ ተመሳሳይ ፡ ዜግነት ፡ ቢኖራት ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የጥንድ ፡ ዜግነት ፡ ችግር ፡ ሳይኖርባት ፡ ግን ፡ ከባሏ ፡ የተለየ ፡ ዜግነት ፡ ከሚኖራት ፡ የበለጠ ፡ ተወዳጃኝነት (ተመራጭነት) ፡ አለው ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ አልተገለጸም ። (ይኸውም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የሚያገባት ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጋ ፡ የውጭውን ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ሳያቀዳጃት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቷን ፡ ይዛ ፡ እንደምትቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ) ። የጥንድ ፡ ዜግነቱ ፡ ችግር ፡ (በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ) ፡ የኢትዮጵያን፡ ዜግነት ፡ ማግኘት ፡ የሌላውን ፡ ዜግነት ፡ የሚያሳጣ ፡ ሁኔታ ፡ በመፍጠር ፡ በቀላሉ ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ።

አንድ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜግነት ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በሕግ ፡ የተጋባች ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሴት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቷን ፡ የምታጣው ፡ የባሏን ፡ ዜግነት ፡ ያገኘች ፡ እንደ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዳግም ፡ መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ የዜግነቱ ፡ ሕግ ፡ አገር ፡ አልባነትንና ፡ ጥንድ ፡ ዜግነትን ፡ ለማስወገድ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሙከራ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የሌላ ፡ ሀገር ፡ ዜግነትን ፡ ብትቀበልም ፡ ሕጉ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቷን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የንብረት ፡ ሕግ ፡ እንደሚገዙ ፡ ያመለክታል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ያለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትዕዛዝ በስተቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ባለቤት ፡ እንዳይሆኑ ፡ ይከለክላል ። ስለዚህም ፡ አንዲት ፡ በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜግነትን ፡ በመቀበል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቷን ፡ ያጣች ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሴት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያላትን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በንጉሠ ነገሥቱ ፡ ትዕዛዝ ፡ መሠረት ፡ ባለንብረትነቷን ፡ ይዛ ፡ እንድትቆይ ፡ ካላስፈቀደች ፡ በስድስት ፡ ወራት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባለንብረትነቷን ፡ መተው ፡ (ከእጆዋ ፡ ማውጣት ፡) የሚኖርባት ፡ ይመስላል ።[24]

## በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ስለሚገኝ ፡ ዜግነት ።

ከ፲፱፻፴ው ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ አስቀድሞ ፡ ለውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ዜግነትን ፡ የመፍቀዱ ፡ ሥልጣን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጠ ፡ ሲመስል ፡ በሥልጣኑም ፡ ለመጠቀም ፡ ነፃነት ፡ የነበረው ፡ ንጉሡ ፡ ነበር ።

የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ሀገር ፡ (በውጭ ፡ ሀገር) ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌለው ፡ አይደለም ። የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ የቅባት ፡ ዜግነትን ፡ የሚመሠክር ፡ ጽሑፍ ፡ ለመስጠት፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ነፃነት ፡ ነበረው ። የታመኑ ፡ የእንግሊዝ ፡ ምንጮች ፡ እንደሚሉት ፡ ስጦታው ፡ (ፈቃዱ) ፡ ጊዜያዊ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ አዘል ፡ ሲሆን ፡ በግልጽ ፡ በሕግ ፡ ከተከለከሉት ፡ መብቶች ፡ ሌላ ፡ የተፈጥሮ ፡ ተወላጆች ፡ የሚያገኟቸውን ፡ መብቶች ፡ በሙሉ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሊያቀዳጃቸው ፡ ይችላል ። የቅባት ፡ ዜግነት ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነድ ፡ (ጽሑፍ) ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ (አቤቱታ) ፡ የቅባት ፡ ዜግነት ፡ ምስክር፡ ወረቀትን ፡ ለማስጠት ፡ የሚያስችሉትን ፡ የሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሊሟሉ ፡ እንዳይችሉ ፡ ወይም ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ እንዳይውሉ ፡ ያደርጋቸውን ፡ ምክንያቶች ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከፈቃዱ ፡ በፊት ፡ መደረግ ፡ ያለበት ፡ ተቀዳሚ ፡ ሁኔታ ፡ የተገዥነት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መግባት ፡ ብቻ ፡ ነው ።[25]

---

23. ሲድለር ፤ እዚያው ፡ ገጽ ፡ ፻፭፩ ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፳፫ ።
24. የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፺፮ ።
25. ኤሊዬንዝ ፡ አንድ ፡ ናሺናሊቲ ፤ ሀልስበሪስ ፡ እስታትዩትስ ፡ ኦቭ ፡ ኢንግላንድ ፡ (፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም.) ፤ ፫ኛ ፡ እትም ፤ ቮል ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፶፪ ።

በኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ፈቃድ ፡ ለውጭው ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ ሲሰጡት ፡ ከሚች ሉት ፡ ከፍተኛ ፡ ክብሮች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ይህንን ፡ ክብር ፡ የሚያቀዳጁት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለአገራቱ ፡ ከፍተኛ ፡ አገልግሎት ፡ ላደረጉ ፡ እንደወሮታ ፡ ነበር ።

ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኝ ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ።[26] ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ የበላይና ፡ ሙሉ ፡ ገዥ ፡ ስለሆን ፡ በሦስት ፡ ሰዎች ፡ በተውጣጣው ፡ ኮሚሺን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተከላከሉ ፡ ሰዎች ፡ ዜግነት ፡ እንዳይሰጥ ፡ የሚከለክ ለው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይኸውም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርዳቸውን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይቅርታንና ፡ ምሀረትን ፡ ለመስጠት ፡ ከሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ (ተነፃፃሪ) ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[27] የኰሚ ሺኑ ፡ ውሳኔ ፡ የመጨረሻና ፡ (አጠቃላይ) ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ የማይባልበ ትም ፡ በመሆኑ ፡ የዜግነቱ ፡ ጉዳይ ፡ ጠንካራ ፡ ምክንያት ፡ አለው ። በሥራ ፡ ላይ ፡ውሎ፡ እንደሚታየውም ፡ በሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ የተውጣጣው ፡ ኰሚሺን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን፡ የተነፈጉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አቤቱታ ፡ (ማመልከቻ) ፡ እያ ቀረቡ ፡ በአንድ ፡ አንድ ፡ አጋጣሚ ፡ ዜግነት ፡ ሊፈቀድላቸው ፡ ተችሏል ።

## <u>ዜግነትን ፡ ስለማጣት ።</u>

አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ዜግነቱን ፡ ሊያጣ ፡ የሚችለው ፡ ሌላ ፡ ዜግነት ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[28] በሌሎች ፡ አቋሞች ፡ እንደሚደረገው ፡ ሳይሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ጠባዩን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ዜግነት ፡ ማሳጣትን ፡ እንደቅጣት ፡ አይወስንም ።[29] ስለዜግነት ፡ ማጣት ፡ በቅባት ፡ በሚገኝ ፡ ዜግነትና ፡ በትውልድ ፡ ዜግነት ፡ መካከል ፡ መለያ ፡ (ልዩነት) ፡ አያደርግም ፡ አንድ ፡ ግለ - ሰብ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን ፡ ካገኘ ፡ ሌላ ፡ ዜግነት ፡ በመቀበል ፡ በፈቃዱ ፡ እስኪተወው ፡ ድረስ ፡ ዜግነቱን ፡ እንደያዘው ፡ ይቆያል ። በርግጥም ፡ የዜግነቱ ፡ ሕግ በግልጽ ፡ መልስ ፡ የማይሰጣቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፡ ያሀል፡ አንድ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ጋር ፡ በመጋባቷ ፡ የቅባት ፡ ዜግነትን ፡ የተቀበለች ፡ የውጭ፡ ሀገር ፡ ሴት ፡ ከጋብቻው ፡ ፍች ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቷን ፡ እንደያዘች ፡ ትቀራለ ችን? ወይም ፡ ባሏ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ ያጣ ፡ እንደሆነ ፡ ይህች ፡ በቅባት ፡ ዜግ ነት ፡ የተቀበለች ፡ ሴት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቷን ፡ እንደያዘች ፡ ትቀራለችን? ሌላ ፡ ዜግ ነት ፡ ካልተቀበለች ፡ ለሁለቱም ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሶች ፡ አወንታ ፡ የሚሆን ፡ ይመስላል ።

## <u>ዜግነት ፡ እንደገና ፡ በድጋሚ ፡ ስለመፈቀዱ ።</u>

የኢትዮጵያ ፡ የዜግነት ፡ ሕግ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ሁለቱ ፡ አንቀጾች ፡[30] ሌላ ፡ ዜግ ነት ፡ በማግኘት ፡ የቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ አጥቶ ፡ እንደገና ፡ (በድጋሚ) ፡ ዜግነት ፡ ስለሚፈቀድለት ፡ ግለ—ሰብ ፡ ይናገራሉ ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡

---

26. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፫ ።
27. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፮ ።
28. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፩ ።
29. ተወላጅነትን ፡ ስለማጣት ፡ ፈረንሣይና ፡ አሜሪካ ፡ የሚከተሉትን ፡ መሥመር ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ የቤድለር ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፲፭—፳፯ ፡ ተመልከት ።
30. የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ እና ፡ ፲፰ ።

ኢትዮጵያ ፡ ተመልሶ ፡ መኖር ፡ ከጀመረና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ካመለከተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነትን ፡ ጥቅም ፡ ሊቀበል ፡ (ሊያገኝ) ፡ ይችላል ።

ዜግነትን ፡ ካጡ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ (በድጋሚ) ፡ ማግኘት ፡ መብት ፡ ይሁን ፡ በችሮታ ፡ መልክ ፡ የሚሰጥ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ከሕጉ ፡ ቋንቋ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። መብት ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማስፈፀም ፡ (በዳኝነት ፡ ለማስከበር) ፡ ያስችላል ፡ ያሰኛል ።[31] ለዚህ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ግልጽ ፡ አንቀጽ ፡ ባለመኖሩ ፡ (ስለሌለ) ፡ መልሱ ፡ የወደፊት ፡ ገለፃን ፡ መጠበቅ ፡ ይኖርበታል ።

ከሕጉ ፡ አግባብ ፡ እንደሚመለከተው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ እንደገና ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ግለ—ሰብ ፡ የቀድሞ ፡ የዜግነት ፡ ምድቡን ፡ እንደያዘ ፡ የሚኖር ፡ ይመስላል ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ቀድሞ ፡ በውልደት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ እንደገና ፡ ዜግነትን ፡ ሲቀበል ፡ በቅባት ፡ ዜግነትን ፡ እንዳገኘ ፡ ሳይሆን ፡ በውልደት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጠራል ። ይህንንም ፡ መገንዘብ ፡ አስፈላጊ የሚሆነው ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ በመኖሩ ፡ ነው ።

<u>በዜጉ ፡ ዜግነትና ፡ በትውልድ ፡ ዜግነት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ።</u>

ማንም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዜጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተገዢ ፡ ተቆጥሮ ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ካሉት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ብዙዎች ፡ ይሰጡታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በትውልድና ፡ በዜጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ በሆኑት ፡ መካከል ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ አንዳንድ ፡ ልዩነታቸው ፡ መኖራቸው ፡ አልቀረም ። እነዚህም ፡ ልዩነቶች ፡ መነሻቸው ፡ የፖለቲካ ፡ መብቶች ፡ ተብለው ፡ መጠራት ፡ በሚገባቸው ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ደንግጓል ።

ከነዚህም ፡ መብቶች ፡ መካከል ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነው ፡ የመምረጥ ፡ መብት ፡ ነው ። ይህም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊነትን ፡ ላገኙ ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል ።[32] ለዚሁ ፡ ደንብ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑት ፡ መንግሥታዊ ፡ ምክንያቶች ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ አይደሉም ። እንደዚሁ ፤ በዜጉ ፡ (ዜጋ) ፡ ተገዢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ኅብረተ ፡ ሰቡን ፡ አጠናቅቆ ፡ በማወቅ ፡ ማንና ፡ ምን ፡ ነገሮች ፡ ለፓርላማ ፡ መቅረብ ፡ እንደሚገባቸው ፡ አመዛዝኖ ፡ የበሰለ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ስለማይችልና ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በቦታው ፡ መቀመጥ ፡ ያለበትም ፡ ሕብረተ ፡ ሰቡን ፡ እንዲያውቅ ፡ እንዲታወቅ ፡ ነው ፡ የሚለውም ፡ ቢሆን ፡ እስከዚህ ፡ የሚገፋፋ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ።

የመምረጥ ፡ መብት ፡ ለሚለው ፡ ተከታይ ፡ የመመረጥ ፡ መብት ፡ ነው ። በዚህ ፡ በኩልም ፡ ቢሆን ፡ ለእማካሪነት ፡ ውድድር ፡ መቅረብ ፡ የሚችሉት ፡ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሆኑ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ አባል ፡[33] ሆኖ ፡ ለመሾምም ፡

31. የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ምሕረቱ ፡ (የተሻሻለው) ፡ የኤርትራ ፡ ዜግነት ፡ ደንብ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚፈለግበትን ፡ ሁሉ ፈጽሞ ፤ የኤርትራ ፡ ዜግነት ፡ እንደገና ፡ ባይሰጠው ፡ የኤርትራ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስተር ፡ የሰጠውን ፡ ይህን ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመቃወም ፡ ለኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ እንዲችል ፡ የደነገገ ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይጠቅማል ።

32. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፤ አንቀጽ ፡ ፺፭ ።

33. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፤ አንቀጽ ፡ ፺፮ ።

እንዲሁ ፣ በትውልድ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ መሆን ፣ ተፈላጊ ፣ ነው ።[34] እንግዲህ ፣ በዜጐ ፣ ዜጎች ፣ የሆኑ ፣ ሁሉ ፣ ከሕግ ፣ አውጭነት ፣ ተግባር ፣ በጥንቃቄ ፣ የተገለሉ ፣ መሆናቸው ፣ ለማንም ፣ ግልጽ ፣ ነው ።

አንድ ፡ የመጨረሻ ፣ ልዩነት ፣ ደግሞ ፣ በዜጉ ፡ ዜጋ ፣ የሆኑ ፣ ሁሉ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፣ የሚኒስትርነት ፡ ማዕረግ ፣ የማግኘት ፡ የማ ይችሉ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ይህ ፡ የሚኒስትርነት ፡ ማዕረግ ፡ የማግኘት ፡ ጉዳይ ፡ ነገሩ ፡ ከሚመለከተው ፡ ሰው ፡ አልፎ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በሚ ያዘው ፡ መሠረት ፡ ሰውየው ፡ በተወለደበት ፡ ወቅት ፡ ወላጆቹም ፡ ጭምር ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ ዜግነት ፡ የነበራቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ፡ ይላል ።[35] ይህም ፡ ማለት ፡ በትውልዱ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ የሆነ ፡ ሰው ፣ ሲወለድ ፣ ሁለቱም ፡ ወላጆቹ ፣ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ ካልነበሩ ፣ ሚኒስትር ፣ ሆኖ ፣ የመሾም ፣ ዕድል ፣ አይኖረውም ። ይህም ፣ የሚ መለከታቸው ፡ ካልተጋቡ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሴትና ፣ የውጭ ፡ አገር ፣ ዜጋ ፣ ከሆነ ፡ ሰው ፡ ተወልዶ ፣ የሰውየው ፡ አባትነት ፡ በሕግ ፡ እንዲፀና ፡ የተደረገለትን ፡ ልጅ ፡ የመሳ ሰሉት ፣ ናቸው ። ስለሆነም ፣ ከሕጋዊ ፣ ጋብቻ ፡ ተወልዶ ፡ እናቱ ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፣ የውጭ ፡ አገር ፣ የነበራት ፣ ሁና ፣ ከላይ ፣ በተጠቀሰው ፣ መሠረት ፣ በቀዋታ ፡ የኢት ዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተሰጣት ፣ ከሆነች ፣ ይህ ፣ ሕግ ፣ በልጁ ፣ ላይ ፣ አይፀናም ።

ምንም ፣ እንኳ ፡ ቀላል ፡ ነገሮች ፡ ባይሆኑም ፡ በትውልድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የሆነውን ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ ከሆነው ፡ የሚለዩት ፡ እነዚህ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ከነሱ ፡ በቀር ፡ ግን ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በብሔራዊ ፡ (ሲቪል) ፡ መብቶች ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያውያን ፣ መካከል ፣ ልዩነት ፡ አይደረግም ፡ ይላል ።[36]

<u>የኤርትራ ፡ አቋም ።</u>

እዚህ ፡ ላይ ፡ በፌዴሬሽኑ ፣ ጊዜ ፣ የኤርትራውያን ፣ ዜጎች ፣ አቋም ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ ብንመለከት ፡ መልካም ፡ ነው ። ይህንን ፣ ኤርትራ ፣ የነበራትን ፡ አቋም ፡ ስናነሳ ፡ የሚያጋጥሙን ፡ ጥያቄዎች ፡ የተወሳሰቡ ፡ ቢሆኑም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ቁም፡ ነገር ፣ የያዙ ፡ ናቸው ። ኤርትራ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አያሌ ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ የተለዋወጡበት ፡ መሆኗን ፡ መገንዘብ ፡ ይረዳል ፤ ባለፈው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጨ ረሻ ፡ ላይ ፡ የጣሊያን ፡ ቅኝ ፡ ሀገር ፡ ከመሆን ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. በእንግሊዝ ፡ የበላይ ፡ ጠባቂነት ፡ አንድ ፣ ግዛት ፡ ወደመሆን ፡ ከዚያም ፡ በ፲፱፻፵፬ ዓ. ም. በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፣ ሥር ፣ ራሷን ፣ ችላ ፡ የፌዴሬሽኑ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ በመሆንና ፤ በመጨረሻም ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ. ም. ከኢትዮጵያ ፣ ጋር ፣ በመዋሐድ ፡ አሁን ፡ ወዳለችበት ፡ ደረጃ ፡ ተላልፋለች ፡[37] ስለዜግነት ፡ በምናወሳበት ፣ ጊዜ ፡ ከነዚሁ ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ የሚያስፈልጉን ፡ የፌዴሬሽኑ ፡ ጊዜና ፡ ከዚያ ፡ ማግሥት ፡ ያለው ፡ አቋሟ ፡ ናቸው ።

---

34. የኢትዮጵያ ፣ የተሻሻለው ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፣ ፯ ።
35. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፣ መንግሥት ፤ አንቀጽ ፡ ፴፫ ።
36. የኢትዮጵያ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፴፫ ።
37. ስለኤርትራ ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ተጨማሪ ፡ ማስረጃዎች ፣ ለማግኘት ፣ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፣ መጽሔት ፣ (፲፱፻፷፰) ዓ ፡ ም ፡) ፤ ቮል. ፩ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፩ ፡ ኢንተርናሺናል ፡ ሎው ፤ እስቴት ፣ ሰክሼሽን ፡ ተብሎ ፡ የተሰ ጠውን ፡ መግለጫ ፡ ተመልከት ።

ኤርትራን ፡ በፌዴሬሽን ፡ ለመቀላቀል ፡ የወጣው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትዕዛዝ ፡[38] እንዲህ ፡ ሲል ፡ ደንግጓል ፡ "የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ የኤርትራ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ትዕዛዝ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ዜጎች ፡ ሆነዋል ።" በተጨማሪም ፡ "በኤርትራ ፡ የተወለዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ወይም ፡ ከአያቶቻቸው ፡ አንዱ ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ ሆኖ ፡ በኤርትራ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡" የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ መሆናቸው ፡ ታውጆአል ። እነዚሀ ፡ ሰዎች ፡ የውጭ ፡ ዜግነት ፡ የያዙ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ "ከዚሀ ፡ በላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ዜግነት ፡ ለመተው ፡ ከዚሀ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ (ትዕዛዙ ፡ የወጣበት ፡ ቀን ፡ ሴፕቴምበር ፡ ፲፩/፲፱፻፶፪) ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጥቷቸዋል ።"[39] ስለዚህ ፡ ማንኛውም ፡ በኤርትራ ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ቢያንስ ፡ አንዱ ፡ አያቱ ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ ከሆንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ አስታውቆ ፡ ካልተወ ፡ (የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነቱን ፡ ለመያዝ ፡ መፍቀዱን ፡ በማስታወቅ) ፡ እንዲሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንደሆነ ፡ ይቆጠራል ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ ፲፱፻፴ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የተወላጅነት ፡ ሕግ ፡ የዩስ ፡ ሳንጉይኒስ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ ብቻ ፡ በቀጥታ ፡ ቢከተልም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትዕዛዝ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይሆን ፡ ሐሳብ ፡ እንድትለውጥና ፡ "በኤርትራ ግዛት ፡ የሚገኙት ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡" የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ከሌላቸው ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ እንዲሆኑ ፡ እንድትፈቅድ ፡ አስገድዶታል ። ይልቁንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ቢያንስ ፡ አንዱ ፡ አያታቸው ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ ከሆኑ ፡ የውጭ ፡ ዜግነታቸውን ፡ ለመያዝ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማስታወቅ ፡ ግዴታቸው ፡ ነበር ፡ ትዕዛዙ ፡ ግን ፡ ማንም ፡ በኤርትራ ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያለው ፡ ዜግነት ፡ እንዳይቀር ፡ አድርጓል ።

ይህ ፡ ትዕዛዝ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተወላጅነት ፡ ለኤርትራ ፡ ነዋሪዎች ፡ ከማጽደቅ ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ተጨማሪ ፡ ወሰን ፡ ባለማድረጉ ፡ በትውልድ ፡ ዜጋ ፡ በመሆንና ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ በመሆን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ለማወቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ፈጥሯል ። የችግሩም ፡ አሳሳቢነት ፡ ልዩነትን ፡ መወሰን ፡ ከሚያስከትለው ፡ የሕግና ፡ የአፈጻጸም ፡ ጉዳይ ፡ የተነሳ ፡ ነው ። ከትዕዛዙ ፡ አሁን ፡ የምንነጋገርበት ፡ ክፍል ፡ ከፌዴራሉ ፡ ደንብ ፡ (አክት) ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የተወሰደ ፡ ሲሆን ፡ በተከታታይነት ፡ የወጣው ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትም ፡ በትውልድና ፡ በዜጉ ፡ ዜግነት ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አያሳይም ፡ ሁሉም ፡ የኤርትራ ፡ ዜጎች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ነበራቸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የመምረጥ ፡ መብትና ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የመሾም ፡ መብት ፡ ነበራቸው ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ አንፃር ፡ ስንመለከተው ፡ ትዕዛዙ ፡ መከፋፈልን ፡ በማስቀረት ፡ በኤርትራውያን ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ እንዳይኖር ፡ አድርጓል ፡ ብለን ፡ መናገር ፡ እንችላለን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተወላጅነት ፡ በትዕዛዙ ፡ አማካይነት ፡ ያገኙ ፡ ኤርትራውያን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ስለነበራቸውና ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የመምረጥና ፡ ሌሎችንም ፡ ስለማያጡ ፡ ሁሉም ፡ በትውልድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ ለመሆን ፡ በቅተዋል ። ፌዴሬሽኑም ፡ የጀመረው ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡

38. የትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፶፪ ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፤ የኤርትራ ፡ ግዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ስለመሠመሩና ፡ ስለመቀላቀሉ ፡ የተሰጠ ፡ ትዕዛዝ ።

39. ሙሉው ፡ የትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ደንብ ፡ አባሪ ፡ ሐ ፡ በመባል ፡ ከዚህ ፡ ጋር ፡ ተያይዟል ።

በፊት ፣ ስለነበር ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፣ ነክ ፣ጭብጦች ፣ ሊነሱ ፣ አይችሉም ። ያም ፣ ሆነ ፣ ይህ ፣ ሁሉም ፣ ሊመጣ ፣ የቻለው ፣ በፌዴራሉ ፣ ደንብ ፣ (አክት) ፣ ስለሆነና ፣ “የተሻሻለው ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፣ ኢትዮጵያ ፣ ተካፋይ ፣ ከምትሆንባቸው ፣ ከኢንተርናሲዮናል ፣ ውሎች ፣ ከዓለም ፣ ስምምነቶችና ፣ ግዴታዎች ፣ ጋር ፣ በአንድነት ፣ ሆኖ ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ መንግሥት ፣ የበላይ ፣ ሕግ ፤” ስለሆነ ፤[40] ሕገ ፣ መንግሥት ፣ ነክ ፣ የሆነ ፣ ችግር ፣ አይፈጠርም ።

በተለይ ፣ መታየት ፣ የሚገባቸው ፣ ሰዎች ፣ ከፌዴሬሽኑ ፣ በኋላ ፣ በዜጉ ፣ የኤርትራ ፣ ዜጎች ፣ የሆኑት ፣ ናቸው ። የ፲፱፻፺፪ቱ ፣ የኤርትራ ፣ ዜግነት ፣ ደንብ ፣ የኤርትራን፣ ዜግነት ፣ እንዴት ፣ ማግኘት ፣ እንደሚቻልና ፣ እንደሚታጣ ፣ ሲወስን ፣ የፌዴራሉ ፣ መንግሥት ፣ ተወላጅ ፣ ሆኖ ፣ መገኘት ፣ በኋላ ፣ የኤርትራን ፣ ዜጋ ፣ ለመሆን ፣ ቀድሞ፣ ተፈላጊነት ፣ ነበረው ። ደንቡ ፣ የኤርትራን ፣ ዜግነት ፣ ለማግኘት ፣ ሦስት ፣ መንገዶች ፣ እንደነበሩ ፣ ይናገራል ። እነሱም ፣ በትውልድ ፣ በስጦታና ፣ በጋብቻ ፣ ናቸው ። በትውልድ ፣ ዜጋ ፣ ነው ፣ የሚባለው ፣ ከሴፕቴምበር ፣ ፲፭/ ፲፱፻፶፪ ፣ በፊት ፣ ኤርትራ፣ ውስጥ ፣ የተወለደ ፣ ያሆንስ ፣ አንዱ ፣ አያቱ ፣ የኤርትራ ፣ ተወላጅ ፣ የነበረና ፣ በፌዴራሉ ፣ ደንብ ፣ አንቀጽ ፣ ፯ ፣ መሠረት ፣ የፌዴራሉን ፣ ተወላጅነት ፣ የተወ ፣ መሆን ፣ አለበት ፣ በሴፕቴምበር ፣ ፲፭/ ፲፱፻፶፪ ፣ ወይም ፣ ከዚያ ፣ በኋላ ፣ ከተወለደ ፣ ግን ፣ በፌዴራሉ ፣ ደንብ ፣ መሠረት ፣ የኤርትራን ፣ ዜግነት ፣ ካገኙ ፣ ወላጆች ፣ የተወለደ ፣ መሆን ፣ ይኖርበታል ። ከኤርትራ ፣ ውጭ ፣ የተወለደ ፣ ከሆነ ፣ በተወለደበት ፣ ጊዜ ፣ ሁለቱም ፣ ወላጆች ፣ የኤርትራ ፣ ዜጎች ፣ የነበሩ ፣ እንዲሆኑ ፣ ያስፈልጋል፤ እሱም ፣ በኤርትራ ፣ ውስጥ ፣ ነዋሪና ፣ ወደ ፣ አገሪቱ ፣ ከገባ ፣ ወይም ፣ ዕድሜው ፣ ሃያ፣ አንድ ፣ ከሆነ ፣ በሁለት ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ ዜግነቱ ፣ ለማግኘት ፣ ማመልከቻ ፣ ያቀረበ፣ መሆን ፣ አለበት ፣ ፌዴሬሽኑም ፣ ከፈረሰ ፣ በኋላ ፣ ያ ፣ ሰው ፣ በትውልድ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜጋ ፣ እንደሆነ ፣ ተቆጥሮ ፣ ማንኛውም ፣ በትውልድ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ የሆነ ፣ ሁሉ ፣ ሊኖሩት ፣ የሚችሉትን ፣ መብቶችና ፣ ግዴታዎች ፣ ያገኛል ።

በስጦታ ፣ ወይም ፣ በጋብቻ ፣ ዜግነቱን ፣ ያገኘው ፣ ሰው ፣ ግን ፣ የሚታየው ፣ ከዚህ ፣ በተለየ ፣ እንጻር ፣ ነው ። የኤርትራን ፣ ዜግነት ፣ ለማግኘት ፣ የፌዴራሉ ፣ ተወላጅነቱ ፣ ቀድሞት ፣ ተፈላጊነት ፣ ስለነበር ፣ በዜጉ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜጋ ፣ ይሆናል። በኤርትራና ፣ (በፌዴሮሽኑ ፣ ሥር ፣ ) ማንኛውም ፣ የኤርትራ ፣ ዜጋ ፣ ሊኖሩት ፣ የሚችሉትን ፣ መብቶችና ፣ ግዴታዎች ፣ የነበሩት ፣ ቢሆንም ፣ እንኳ ፣ ከአንድነቱ ፣ በኋላ፣ ሊያገኝ ፣ የሚችለው ፣ መብትና ፣ ግዴታዎች ፣ እንዳንድ ፣ በዜጉ ፣ የኢትዮጵያ ፣ ዜጋ፣ እንደሆን ፣ ሰው ፣ ሆኖ ፣ ነው ። የኤርትራ ፣ አቋም ፣ አንዳንድ ፣ ጥያቄዎችን ፣ ለማስነሣት ፣ የቻለው ፣ ኢትዮጵያና ፣ ኤርትራ ፣ ተወላጅነትን ፣ በማግኘትና ፣ ይልቁንም ፣ በመብት ፣ አጠቃቀም ፣ በኩል ፣ በጣም ፣ የተለያየ ፣ መንገድ ፣ ስላላቸው ፣ ነው ።

## ማጠቃለያ ፣ ሐሳቦች ።

በአጭር ፣ አነጋገር ፣ ተወላጅነትን ፣ በትውልድ ፣ ለማግኘት ፣ ሁለት ፣ መንገዶች፣ ሲኖሩት ፣ ኢትዮጵያ ፣ የምትከተለው ፣ የዩስ ፣ ሳንጉይኒስን ፣ መሠረት ፣ ሐሳብ ፣ ብቻ፣ ነው ። በጠቅላላው ፣ ግን ፣ ዜግነት ፣ አልቦ ፣ መሆንና ፣ ተደራራቢ ፣ ዜግነትን ፣ የመያዝ ፣ ችግር ፣ እንዳይፈጠር ፣ ኢትዮጵያ ፣ የተከተለችው ፣ መንገድ ፣ መልካም ፣ ነው። ስለሆነም ፣ የ፲፱፻፴፪ው ፣ የተወላጅነት ፣ ደንብ ፣ ከአዲሶቹ ፣ ሕጎቻችን ፣ ጋር ፣ በማዛመድ ፣ መሻሻል ፣ ያስፈልገዋል ።

40. የኢትዮጵያ ፣ የተሻሻለው ፣ ሕገ ፣ መንግሥት ፤ አንቀጽ ፻፳፪ ።

ከመሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹም ፡ ቢሆን ፡ ጥቂት ፡ ለውጥ ፡ ያስፈ ልጋቸዋል ። ለምሳሌ ፡ ጉዲፈቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ደንብ ፡ የልጁን ፡ ተወላጅነት ፡ በምንም ፡ አይለውጠውም ። ይህም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ልጅ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ በጉዲፈቻ ፡ ቢወሰድም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንደሆነ ፡ ይቀራል ፤ የሰውዬው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ልጅ ፡ የዚያን ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ነት እንዳገኘ ፡ ቢቆጥረውም ፡ እንኳ ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም ፡ በሌላ ፡ አንፃር ፡ ደግሞ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅነት ፡ የያዘው ፡ ልጅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ አድርጎት ፡ ልጁ ፡ የያዘውን ፡ ተወላጅነት ፡ ቢያጣም ፡ በለውጡ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተወላጅነት ፡ አያገኝም ፡ ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ፡ በዋለ ፡ ጊዜ ፡ ዜግነት ፡ አልባ ፡ መሆንና ፡ ተደራራቢ ፡ ዜግነትን ፡ ለማስወገድ ፡ ይህን፡ ሕግ ፡ ከጠቅላላው ፡ ዓላማና ፡ ዜግነትን ፡ መልሶ ፡ ለመስጠት ፡ ከወጣው ፡ ደንብ ፡ ጋር፡ አስተባብሮ ፡ ጥቂት ፡ መለወጥ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ይህም ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጆችን ፡ ዜግነት ፡ አልባ ፡ ከመሆን ፡ ወይም ፡ ተደራራቢ ፡ ዜግነትን ፡ ከማግኘት ፡ ያድናቸዋል ። ተደራራቢ ፡ ተወላጅነት ፡ የሚባለው ፡ አንዲት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ያላት ፡ ሴት፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ባገባች ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተወላጅነት ፡ በቀጥታ ፡ ሲሰጣት ፡ የሚመጣ ፡ ነገር ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዜጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በሆነ ፡ ሚስቱና ፡ ልጆቹም ፡ በዜጉ ፡ ዜግነት ፡ ካላገኙ ፡ በስተቀር ፡ ዜግነት ፡ አልባ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ባገሩ ፡ ከተወለደ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ስለሚያሰጥ ፡ ልዩነት ፡ አለ ፡ ቢባል ፡ ፕሬዚደንትና ፡ ምክትል ፡ ፕሮዚደንት ፡ ሆኖ ፡ ለመመረጥ ፡ የሚችለው ፡ በዚያው ፡ አገር ፡ የተወለደ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ።[41] በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ግን ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀት ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲወለድ ፡ ጀምሮ ፡ የእንግሊዝ ፡ ዜጋ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ባለበት ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ የፖለቲካም ፡ ሆነ፡ ሌላ ፡ መብቶችና ፡ ሥልጣኖች ፡ ይኖሩታል ፤ ግዴታና ፡ ተግባሮችም ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ናቸው ።[42] እንዲህ ፡ ሲባል ፡ ግን ፡ በየትም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ተመሳሳይ ፡ አቋም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ አይደለም ። የ፲፭ኛው ፡ መቶ ፡ የእስፓኝ ፡ ሕጐች ፡ በኢንኩዚሽኑ ፡ (inquisition) ተመርተው ፡ ሙሉ ፡ ዜግነትን ፡ ለማግኘት ፡ ክርስቲያን ፡ መሆን ፡ ተፈላጊ ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር ። ባለፈው ፡ ክፍለ ፡ ዘመንም ፡ በፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ደምበኛ ፡ ዜግነትን ፡ (citoyen) የሚያሰጥ ፡ ሙሉ ፡ በዜጉ ፡ ዜግነትና ፡ (la grande nationalization) የመምረጥ ፡ መብት ፡ ያልተሰጠው ፡ መጠነኛ ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ፡ (la petit nationalization) የሚል ፡ የመለያየት ፡ ዝንባሌ ፡ ተጀምሮ ፡ ነበር ።[43]

የአንድ ፡ አገር ፡ ዜጋዎችን ፡ መካፈል ፡ ከልክ ፡ አልፎ ፡ የሄደው ፡ ሂትለር ፡ ባወጣቸው ፡ የኑርምበርግ ፡ ሕጐች ፡ አማካይነት ፡ ነበር ። በነዚህም ፡ በዜግነት ፡ የመበላለጥ ፡ ደረጃ ፡ ተፈጥሮ ፡ ገሚሶቹ ፡ እንዲሁ ፡ ያገሩ ፡ (Reich) ተወላጅ ፡ ብቻ ፡ ሲባሉ ፡ የቀሩት ፡ የተለየ ፡ የዘር ፡ ብልጫ ፡ ያላቸው ፡ ደግሞ ፡ ሙሉ ፡ የሆነ ፡ የዜግነት ፡ ደርጃ ፡ ነበራቸው ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ የፖለቲካ ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሕ

---

41. ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኮንስቲትዩሽን ፤ አርቲክል ፡ ፪ ፡ ሴክሽን ፡ ፩ ፤ አሜንድመንት ፡ ፲፪ ፤ እና ፡ ናሽናሊቲ ፡ አክት ፡ ኦፍ ፡ ፲፱፻፵ ።
42. ኦሊዩንዝ ፤ ሐልስበሪስ ፡ ኢስታትዩትስ ፡ ኦፍ ፡ ኢንግላንድ ፡ (፲፱፻፵፰ ፤ ፪ኛ ፡ እትም) ፤ ቮል. ፩ ፡ ገጽ ፡ ፲፻፴፪ ።
43. ኤም ፡ ኬስለር ፤ ስብጄክት ፡ ሲቲዝን ፡ ናሺናል ፡ አንድ ፡ ፐርማነንት ፡ አሊጂንስ ፤ ዬል ፡ ሎው ፡ ጆርናል ፡ (፲፱፻፵፮—፵፯) ቦል- ፶፮ ፡ ገጽ ፡ ፰፯ ።

ይወታቸው ፡ ነፃነታቸውና ፡ ንብረታቸውም ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑትን ፡ ሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ ተነፍገው ፡ ነበር ፡ በአለንበት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ አንደኛና ፡ ሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያላቸው ፡ ዜጎች ፡ እያሉ ፡ መከፋፈል ፡ ተፈላጊ ፡ አለመሆኑን ፡ ተገንዝበናል ፡ አሁን ፡ የሚደረግ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ መከፋፈል ፡ ማቆሚያ ፡ ለማይገኝለትና ፡ ብዙ ፡ ጉዳትን ፡ ለሚያስከትል ፡ መድሎ ፡ መግቢያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ዕድል ፡ ያላጋጠመውን ፡ ያንዱን ፡ ክፍል ፡ ደህንነት ፡ የፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ ባገኙት ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ በዘፈቀደ ፡ እንዲያዙበት ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በተለዩም ፡ ያገር ፡ ውስጥና ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ፀጥታ ፡ በደፈረሰባቸው ፡ ወቅቶች ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የእምነት ፡ ማጣት ፡ ነፃነቱ ፡ ያላግባብ ፡ እንዲወሰንበት ፡ ያስደርጋል ።[44]

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ፡ ከጥቂት ፡ የፖለቲካ ፡ መብቶች ፡ በስተቀር ፡ ማንኛውም ፡ ዜጋ ፡ ሊኖረው ፡ የሚገቡትን ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ ይሰጣል ። እነዚህም ፡ የቀሩት ፡ ጥቂት ፡ መብቶች ፡ የመምረጥና ፡ ማዕረግ ፡ የማግኘት ፡ መብቶች ፡ ተብለው ፡ ሊለዩ ፡ ይችላሉ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ሚኒስትሮችንና ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ አባሎችን ፡ የመሾም ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ይልቁንም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እነዚህን ፡ ማዕረጎች ፡ ለማግኘት ፡ መብቱ ፡ አድርጎ ፡ መጠየቅ ፡ ስለማይችል ፡ በትውልድ ፡ ዜጋ ፡ የመሆን ፡ ተፈላጊነት ፡ እንደትልቅ ፡ ነገር ፡ በመቁጠር ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ አንቀጽ ፡ ሰጥቶ ፡ መናገሩ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ አይመስልም ፡ የመምረጥ ፡ መብትን ፡ ያህል ፡ መሠረታዊ ፡ ነገር ፡ በዲሞክራሲ ፡ አገዛዝ ፡ በሚመራ ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ከዜጋዎቹ ፡ ላንዱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ መነፈጉም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ የለውም ።

በኢንተርናሲዮናል ፡ ደረጃ ፡ ስለሚያጋጥሙን ፡ ችግሮች ፡ ስንመለከት ፡ ደግሞ ፡ የወደፊቱ ፡ ዓለም ፡ ሕጋዊ ፡ ተወላጅነት ፡ የሚለውን ፡ ሐሳብ ፡ ለማስቀረት ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ። ስለሆነም ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ሕግ ፡ ተወላጅነትን ፡ በማግኘትና ፡ በማጣት ፡ ጉዳይ ፡ የበላይነት ፡ ኖሮት ፡ የያንዳንዱ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ ያላቸውን ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያሳጣቸው ፡ ይታመናል ። እንደዚሁም ፡ ለወደፊቱ ፡ ከትውልድ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ከዘር ፡ ይልቅ ፡ ምንባር ፡ ተወላጅነት ፡ ማግኘትንና ፡ ማጣትን ፡ ቢወሰን ፡ የተሻለ ፡ ነው ።[45]

---

44. ሽናይደርማን ፡ ሸርሰሰ ፡ ጂ ፡ ኢስ ፡ ኤ ፤ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ሱፕሪም ፡ ኮርት ፡ ሪፖርት ፡ (፲፱፻፵፫፡ዓ፡ም፡) ቮል. ፫፻፳ ፡ ገጽ ፡ ፻፲፰ ።
45. ኪስለር ፡ እዚያው ።

## አባሪ ፡ ሀ

## የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ የሚችልበት ፡ ዐዋጅ ፡*

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

### ዐዋጅ ።

የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ሆኖ ፡ ለመቆጠር ፡ ለሚገባው ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ አቁመናል ።

በውጭ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ስለተወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ዜግነት ።

፩) በኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ካንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ ካንዲት ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ የተወለደ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ በሚጋቡበት ፡ ጊዜ ፡ የዜግነት ፡ ጉዳይ ።

፪) አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ በሥርዓት ፡ የተጋባ ፡ እንደሆነ ፡ ሴትዮዋ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ትሆናለች ።

፫) ይህን ፡ በመሰለ ፡ ጊዜ ፡ በሥርዐት ፡ የተደረገ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ጋብቻ ።

ሀ) አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ካንዲት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጋብቻ ፡ ልማድ ፡ በባለኵል ፡ ደንብ ፡ (ሲቪል) ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚደረገው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ።

(ለ) አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ካንዲት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ በተጋቡበት ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው ፡ የጋብቻ ሥርዓት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚደረገው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ።

፬) አንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ካንድ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በሥርዐት ፡ የተጋባች ፡ እንደሆነ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመጋባቷ ፡ ምክንያት ፡ የባሏን ፡ ዜግነት ፡ የምትይዝ ፡ የሆነች ፡ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መሆንዋ ፡ ይቀራል ። የጋብቻዋ ፡ ሥርዓት ፡ የባሏን ፡ ዜግነት ፡ የማይሰጣት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንደሆነች ፡ ትቀራለች ። ነገር ፡ ግን ፡ በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነችው ፡ ሴት ባለርስት ፡ የሆነች ፡ እንደሆነ ፡ የርስቷ ፡ ነገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ባቈመው ፡ የርስት ፡ ደንብ ፡ ይጨረሳል ።

፭) ይህን ፡ በመሰለ ፡ ጊዜ ፡ በሥርዓት ፡ የተደረገ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠረው ፡ ጋብቻ ፡

(ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ ካንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በባሏ ፡ ቆንሲል ፡ ፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የምታደርገው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ።

(ለ) የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ ካንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ባሏ ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ጋብቻውም ፡ በሚፈጸምበት ፡ አገር ፡ እንደሚደረገው ፡ የሕግ ፡ ሥርዓት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የምታደርገው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ።

ከኢትዮጵያውያንና ፡ ከውጭ ፡ አገር ዜጎች ፡ በጋብቻ ፡ የሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ ዜግነት ።

፮) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ክፍል ፡ እንደተነገረው ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በሥርዐት ፡ ተጋብተው ፡ ልጆች ፡ የወለዱ ፡ እንደሆነ ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ያባታቸውን ፡ ዜግነት ፡ ይይዛሉ ። ስለሆነ ፤ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ፈጽመው ፡ ከተጋቡ ፡ ካንድ ፡ ኢትዮጵያዊና ፡ ካንዲት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሴት ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ የናቱን ፡ የቀድሞ ፡ ዜግነት ፡ አለመያዙን ፡ ሥልጣን ፡ ባላቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሹማምንቶች ፡ ፊት ፡ ተጠይቆ ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

፯) የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ፈጽመው ፡ ከተጋቡ ፡ ካንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሴትና ፡ ካንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ካባቱ ፡ ዜግነት ፡ መውጣቱን ፡ አስመስክሮ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ሊመለስ ፡ ይችላል ።

---

*ዝክረ ፡ ነገር ፤ ከባላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፤ ከገጽ ፡ ፰፻፮—፱፻፪ ።

ከኢትዮጵያውያንና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ከጋብቻ ፡ በፊት ፡ ስለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ዜግነት ።

፰) አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከወለዱ ፡ በኋላ ፡ እንዳባትየው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ በሥርዐት ፡ የተጋቡ ፡ እንደሆነ ፤ ደግሞ ፡ ያባትየው ፡ አገር ፡ ሕግ ፡ ልጁን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሚያደርገውና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋም ፤ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ የሚቀበለውን ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ የሚያሳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከጋብቻ ፡ በፊት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ያባቱን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ይይዛል ። በዜግነቱ ፡ የሚቀበለውን ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነቱን ፡ ጠብቆ ፡ ይኖራል ።

እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ካልተጋቡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰውና ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሴት ፡ ስለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ዜግነት ።

፱) አንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ ሳይጋቡ ፡ ልጅ ፡ የወለዱ ፡ እንደሆነ ፡ የውጭው ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢቀበለውም ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ያባትየው ፡ አገር ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ ለልጁ ፡ ያባቱን ፡ ዜግነትና ፡ ዜጋ ፡ በመሆን ፡ ምክንያት ፡ የሚቀበለውን ፡ ሥልጣኑ ፡ ሁሉ ፡ የሚያገኝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መሆኑ ፡ ሊቀርበት ፡ አይችልም ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ስለሆነ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ልጅ ፡ ዜግነት ።

፲) የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንዳገራቸው ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፡ ጥጋሰ ፡ አድርገው ፡ ያሳደጉ ፡ እንደሆነ ፡ የልጁ ፡ የቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይለወጥም ።

የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ ስለማጣት ።

፲፩) (ሀ) አንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመጋባቷ ፡ ምክንያት ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ ሁና ፡ ልትቆጠር ፡ የተገባት ፡ እንደሆነ ።

(ለ) አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ዜግነቱን ፡ ለውጦ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መሆኑ ፡ ይቀራል ።

በዜጉ ፡ ዜጋ ፡ መሆን ።

፲፪) (ሀ) እንዳገሩ ፡ ሕግ ፡ በፈቃዱ ፡ አዳሪ ፡ ለመሆን ፡ ወደሚችልበት ፡ ዕድሜ ፡ የደረሰ ።

(ለ) ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኖረ ።

(ሐ) ለሕይወቱና ለራሱ ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ የሚችል ።

(መ) ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገርና ፡ የሚጽፍ ።

(ሠ) ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ በኃጢአት ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ያልተፈረደበት ፡ መሆኑን ፡ የሚያስመሰክር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

፲፫) የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልገውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጥያቄውን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያቀርባል ፤ ከዚህም ፡ ጥያቄ ፡ ጋራ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ የሚመሰክርለትን ፡ ወረቀትና ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ተከሶ ፡ እንደሆነ ፡ የተፈረደውን ፡ ነገር ፡ የሚያበረዳ ፡ የፍርድ ፡ ወረቀቱን ፡ ጨምሮ ፡ ያቀርባል ።

፲፬) በተለየ ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትርና ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሌላም ፡ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ባንድነት ፡ ሁነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ከሚጠይቀው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በቀጥታ ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ ፡ ጥያቄውን ፡ ተመልክተው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ምርመራ ፡ አድርገው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ እንዲሆን ፡ ይፈቅዱለታል ፤ ወይም ፡ ይከለክላል ።

፲፭) ዜግነቱንም ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ (በዲክሬ) ፡ ይቀበላል ፤ አዲሱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በነ ዚሁ ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ እንዳይከዳ ፡ ይምላል ።

፲፮) የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አደራረግ ፡ የተቀበለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ ይረጋል ፡ እንጂ ፡ ሚስቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ካልጠየቀች ፡ በቀር ፡ አስቀድሞ ፡ የያዘችውን ፡ ዜግነት አይለውጠውም ።

የኢትዮጵያን ፡ ዜግነት ፡ እንደገና ፡ ስለማግኘት ።

፲፯) አስቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ የነበሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመኖር ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ለመመለስ ፡ ከመንግሥት ፡ የጠየቁ ፡ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

፲፰) ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በመጋባቷ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ መሆንዋ ፡ የቀረ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሴት ፡ ከባሏ ፡ ተፋታ ፡ ወይም ፡ ባሏ ፡ ሙቶባት ፡ ጋብቻዋ ፡ ፈርሶ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ በመለያየቷ ፡ ምክንያት ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ተመልሳ ፡ የተቀመጠች ፡ እንደሆነና ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ልሁን ፡ ብላ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የጠየቀች ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ ትችላለች ።

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስለ ፡ ዜግነት ፡ ነገር ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ያፈርሳል ።

ሐምሌ ፡ ፲፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

## አባሪ ፡ ለ

በሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ዜግነት ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ የሚያሻሽል ፡ ዐዋጅ ።

በሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በ፩ኛው ፡ ክፍልና ፡ ስለዜግነት ፡ ነገር ፡ በሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመት በወጣው ፡ ሕግ ፡ ባ፲፪ኛው ፡ ክፍል ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ ባዋጅ ፡ አውጥተናል ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ የሚጠይቅ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የሚጠቅም ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጠያቂውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ አድርጎ ፡ ለመቀበል ፡ ሌላ ፡ የተለየ ፡ ምክንያት ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ ለመሆን ፡ የሚጠይቅ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ከዚህ በላይ ፡ በተባለው ፡ በዜግነት ፡ ሕግ ፡ ባ፲፪ኛው ፡ ክፍል ፡ (ለ ፡ መ) ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፉትን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችልም ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ።

መስከረም ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ·

*ዝክረ ፡ ነገር ፡ ባላ. ማ. ሥ. ወ. መ. — ገጽ ፡ ፱፻፪ ።

## አባሪ ሐ ።

ቁጥር ፡ ፮ ፡ ፲፱፻፵፬ ።

ትዕዛዝ ።

የኤርትራ ፡ ግዛት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ስለመጨመሩና ፡ ስለመቀላቀሉ፡ የተሰጠ ፡ ትዕዛዝ ፡ ክፍል ፡ ፱ ፤ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ የኤርትራ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ትዕዛዝ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ዜጎች ፡ ሆነዋል ። በኤርትራ ፡ የተወለዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ወይም ፡ ከአያቶቻቸው ፡ አንዱ ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጅ ፡ ሆኖ ፡ በኤርትራ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ ዜጎችና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ናቸው ።

ስለሆነ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ሰው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነት ፡ ይዞ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተሰ ጠውን ፡ ዜግነት ፡ ለመተው ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጥቶታል ። መተ ውን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሳያስታውቅ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜግነቱን ፡ ያጣል ።